

# ድልን በትግል!

ከሂሩት ድንቅነህ ኖርዌይ ኦስሎ

የኢትዮጵያውያን ደም በከንቱ ፈሶ እንዳይቀር፣ ወንጀለኞቹ ለፍርድ እንዲቀርቡ በአንድነት ሊለውጥ እንኳ እንደህዝብ ለህዝብና ለሐገር የሚያስብ ሐገርንና ህዝብን ማስተዳደር የሚችል ድርጅትን ወይም ፓርቲንና መሪን ፈልጎ ማግኘት የኛ የህዝቦቹ ድርሻ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል:: ለሰብዓዊ መብት በሚቆረቆሩና ሰባዊ መብትን በሚረግጡ መሀል ያለው ፍልሚያ በሺሕ የሚቆጠሩ ንፁሀን በየእስር ቤቱ እንዲታጎሩ ሲያደርግ የዛኑ ያህል ደግሞ ክቡር ህይወት እንዲያልፍ ምክንያት ሆኖ በግፍ የሚሰቃየውና ሐገሩን ጥሎ የሚሰደደውን ደግሞ ቤት ይቁጠረው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ ለማምጣት የምናደርገው ትግል፡ ልዩነቶቻችንን አሁን የምናጎላበት ሳይሆን በግልጽ ለእውነተኛ ለውጥ የምንተጋበት አዲስ አቀራረብና ስልት ይሻል። ብዙዎች አበክረው እንደሚናገሩትና ሁላችንም እንደምናምነው ትግላችንን የሚቃኙት ዋናዎቹ ርእዮታችን በሁለት መሰረታዊ ፍልስፍናዎች ላይ መሰረት መጣል አለባቸውም።

አንደኛ ነገር፡ ሰብአዊነታችን፡ ወይንም ሰው መሆናችን ከጎሳችን፡ ከብሄራችን፡ ከዘራችን ከሀይማኖታችን ከአፍሪካዊነታችን፡ ይቅደም። ሁለተኛ ነገር፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ሁላችንም አብረን ነጻ ካልወጣን፡ ማንም እውነተኛ አርነት አይወጣም። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ነጻ አልወጣችምና የትግራይ ነጻነት ግንባር አርነት ብሎ ይነሳ እንጂ፡ ያ የተነሳበትን አርነት ገና ህዝቡ አልደረሰበትም ። ነገም የአገሌ ነጻ አውጪ፡ የእንቶኔ ነጻነት ግንባር ብለን ብንነሳ፡ ኢትዮጵያ ነጻ እስካልወጣች ድረስ፡ እውነተኛ የአገሌ የእንቶኔ ነጻነት አይኖርም።

ሁላችንም ባርነት ውስጥ ነው ያለነው:: ለነዚህ ሁለት መሰረታዊ መርሆች የተገዛን እለት ነው ሁላችንም አሸናፊ የምንሆነውና ተሸናፊ የማይኖረው። የናፈቀንም አሸናፊና ተሸናፊ የሌለበት፡ የምናሸንፈው ዋናውን ጠላት ድንቁርናና አምባገነንነትን ብቻ የሆነበት አገር ወይም አለም ማግኘት ነው። ይህንንም ከግብ ለማድረስ ኢሕኣፓ የሕዝቦችን የመብትና የነጻንት ጥያቄ አንግቦ ለፍትህ ዲሞክራሲና እኩልነት ሲታገል ኣራት ኣስርተ ኣመታት ኣልፈዋል፥ አሁንም እየታገለና እየጣረ ይገኛል።

በብዙ አቅጣጫ እና መልኩ ኢትዮጵያ በሉአላዊነቷ ከፍ እስክትልና ነፃነቷን እስክትቀዳጅ ድረስ በየወቅቱ ከትግል ተሞክሮው አካሔዱን እና የፖለቲካ አቋሙን እያሻሻለ ወደፊት በመገስገስ የህዝብን ንቃት ህሊና በሚኮረኩረው የዳበረ ዕውቀቱ ለተጨቆነው እና ፍትህ እና ርትዕ ላጣው ወገን ህይውቱን በመስጠት በመደጋገም

ሰብዓዊነት ደብዛው ጠፍቶ በእንቆቅልህ ምንአውቅልህ አይነት ጨዋታ ለዜጋው የህልም አለም ሆኖ እኩልነት፣ ሰላም፣ ልማት እና ዲሞክራሲ የወረቀት ማድመቂያ ቃላቶች ከሆኑ ምንም ትርጉም የላቸውም በማለት እያወጀ በፍትህ ጥያቄ ለተሞላ ህዝብ ጥያቄውን በተገቢው መልኩ ሳይመልሱ ለተጨማሪ ጭቆና መንደርደሩ የወንጀሎች

ሁሉ ቁንጮ መሆኑን እያስተማረ እንዲሁም ወያኔ ከፓርላማ እስከ ወረዳ ፍርድ ቤቶች በሁሉም ቦታዎችና በሁሉም ጊዜያት የዘረኛ አገዛዙ መሣሪያ በማድረግ የተከበረችው ፍትህን እንዳረከሰ በድፍረት እየመሰከረ ስለ መፍትሔውም ብዙ የሚያነሳቸው የትግል ስልቶች ቢኖሩትም ይህንን ብቃቱንን እና ሙሉ ጉልበቱን የሚያውለው በቂ ምክንያቴ ለሚለው የወያኔን እድሜ ማሳጠር ወያኔ በየሰከንዱ የሚተነፍሰው እያንዳንዱ እስትንፋስ ፍትህን ገዳይ ኢትዮጵያን ይበልጥ የሚያረክስ መሆኑን ጠንቅቆ ስለሚያውቅም ጭምር ነው፡፡

በኢትዮጵያ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ለመመስረት የምንችለው ኢትዮጵያውያን እራሳችን ነን፡፡ እንደ አንድ ሕዝብ ተደራጅተን የሀገራችንንን ጠላት ከነግሳንግስ አስተዳደሩ ለመንቀል ሳንያያዝ እና እንደሚገባ ሳንታገለው ጨቋኝ ስርዓቱ እንዲኖር እና አመታት እንዲቆጥር ያደረግነው እኛው ራሳችን ነን። ስለዚህም እኛው ነንም ስርዓቱ ለሕዝብ ጥቅምና አገልግሎት አንዲሆን ማድረግ የምንችለው፡፡ እርግጥ እኛ ኢትዮጵያውያን ፈርሃ እግዚአብሔር እንዳለብን ይታወቃል። ይህ አይነቱ የሞኞች ጨዋነትም የጎዳን ጨላማውን ጨለማ ብርሀኑን ብርሀን ብለን የማንናገርም የሀይማኖት ካባ ለባሾች ብቻ ስለሆንንም ጭምር ነው። ህዝባችን በረሃብ እንዲረገፍ፡ ብዙ ዜጎች በደርግ በሻአብያና ወያኔ እንዲገደሉም ተደርጎአል፡፡ ይህ አረመኔ ቡድን የገደላቸውንና ያስገደላቸውን ንፁሃን ዜጋዎች እኛ ብንጠነክር እና ብንያያዝ ባልተገደሉ። ወያኔና ግብረአበሮቹም በኛ የበረታ ጉልበት ለፍርድ አቅረብን ሌሎች የኢትዮጵያን ሉዐላዊነት የሚያስጠብቁቱ መሪዎች አንዲመሩን ባደረግን ነበር። ግን እስካሁን ምንም የተደረገ ነገር የለም። አሁንም ለተጨማሪ አምስት አመታት ሀገሪቷን ሊይስቆለቁሉ እየተንደረደሩ ነው፡፡

በእርግጥም በኢትዮጵያ ውስጥ የሰፈነው ግድያ፡ ስቃይ፡ ሰብአዊ መብት ገፈፋ፡ ሙስና መቆም አለበት። ትግላችን ግቡን የተራዘመበት አንዱ ምክንያት የሙሉ ጊዜ ጠላትን በትርፍ ጊዜ የመዋጋት ወይም የመታገል ስሜት የተጠናዎታቸው በየወቅቱ የሚፈጠሩ አላስፈላጊ ድርጅት ወይም ግንባር ነን ባዮች ናቸው። ብዛት የማሸነፍ ወይም ለማሸነፍ ወሳኝ አይደለም፤ ይልቅስ በህዝብ ህሊና ውስጥ ሰደድ እሳት ለመለኮስ የሚተጉ የማይደክማቸውና የተቆጡ ጥቂቶች እንጂ። በየጊዜውና በየወቅታዊ ክስተቶች ለጥቅም ይሁን ለደባ በማይገባ መልኩ መሰረታቸውና አወቃቀራቸው ለይድረስ ይድረስ፥ ለይስሙላ በሆኑ ድርጅቶች ትግሉ አንዲራዘም አለያም ሕዝባችን እንዲወነዣበር ከማድረጋቸው ውጪ የፈጥሩት ፋይዳ የለም።

ደማችን በከንቱ ፈሶ እንዳይቀር፣ ወንጀለኞቹ ለፍርድ እንዲቀርቡ በአንድነት ለለውጥ መነሳት አለብን። ማንኛውም ትግል መስዋእትነት ይጠይቃል፥ ለዚህም በታጋይ ልጆችዋ ደም መስዋዕትነት የተጀመረው ትግል ግብ ደርሶ ለበርካታ ኣመታት አየተፈራረቁ ለሚወራጩ እጃቸው በደም የራሰ አምባገነኖችን ለፍርድ በማቅረብ ሕዝባችን እፎይ ብሎ ኑሮውን፥ እምነቱን፥ ባህሉን ሆኖ የሚኖርበትን ዘለቄታዊ ሁኔታ መፍጠር የዚህ ትውልድ ግዴታ ነውና በአንድነት ለለውጥ አንነሳ። እንታገል።

ኢትዮጵያችን ለዘላለም ትኑር።

እናቸንፋለን !!!